**የወልቃይት ባህልና የማንነት ጥያቄ**

በወልቃይት ህዝብ ላይ የዘር ማጥፋት ወንጀል ተፈጽሟል የሚሉ አካላት ከሚያቀርቧቸው ምክንያቶች አንዱ የወልቃይትን ባህል ለማጥፋት በትግራይ ነጻ አውጭ ድርጅት የተቀናጀና የተቀነባበረ ዘመቻ በመካሄድ ላይ ነው የሚል ነው። በቅርቡ "ከትግራይ ጋር በባህል፣ በታሪክ፣ በስነልቦናና በመሳሰሉት ዋና ዋና የማንነት መስፈርቶች አንገናኝም " በማለት የወልቃይት አማራ ማንነት አንግበው የተነሱ ሰዎች ከሚጠቅሷቸው መከራከሪያ ነጥቦች አንዱ ባህል እንደሆነ በግልጽ ተቀምጧል። አንድን ብሄር ወይም በሶስተኛው አለም አውድ፣ አንድን ብሄረሰብ፣ ብሄረሰብ የሚያሰኙት የሚከተሉት መስፈርቶች ናቸው። አንደኛ፣ በታሪክ አጋጣሚ በመተቃቀፍ አብሮ የሚኖርና የተረጋጋ ማህበረሰብ፣ ሁለተኛ፣ አንድ ዓይነት የመግባቢያ ወይም የጋራ መነጋገሪያ (ቨርናኪውላር) ቋንቋ ያለው፣ ሶስተኛ፣ በአንድ የተካለለ መልክአ ምድራዊ ይዞታ የሚኖር፣ አራተኛ፣ ከተዋሃደ ምጣኔ ሃብታዊ ትስስር ደረጃ ላይ የደረሰ፣ አምስተኛ፣ በባህሉ አማካኝነት የሚገለጽ ተመሳሳይ ስነ ልቦናዊ ባህርይ ያለው።

ከላይ ከተጠቀሱት አምስት መስፈርቶች ውስጥ ቋንቋ አንዱ ነው። የወልቃይት አካባቢ ወደ ትግራይ የተከለለው ቋንቋን ሰበብ በማድረግ ነው። ሌሎች መስፈርቶችን ግምት ውስጥ ባለማስገባት የሚደረግ አከላለል ደግሞ ችግር አለው። አንድ ዓይነት ቋንቋ የሚናገሩ ሁሉ በአንድ ብሄረሳብ ይጠቃለላሉ ማለት አይደለም። ለምሳሌ ያህል እንግሊዛዊያንና አሜሪካዊያን የአንድ ቋንቋ ማለትም የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተናጋሪ ናቸው፣ ነገር ግን አንድ ብሄር አይደሉም። ስለዚህ የተለያዩ ብሄረሰቦች የተለያዩ ቋንቋዎች መናገር ይኖርባቸዋል ማለት አይደለም። በአንጻሩ፣ እያንዳንዱ ብሄረሰብ የራሱ የሆነ አንድ የጋራ መነጋገሪያ ቋንቋ ብቻ ነው ሊኖረው የሚችለው። ብሄራዊም ሆነ የስራ ቋንቋ ወይም በጉርብትና ምክንያት የሚነገር ቋንቋ አንድን ብሄር ከሚገልጹ መለኪያዎች ውስጥ አይካተትም። ብሄረሰቡ በዋናነት በእለታዊ ግንኙነቱ የሚነጋገርበት ወይም ቨርናኪዩለር መሆን አለበት። በዚህ አገባቡ ስንመለከተው ወልቃይቴዎች ትግርኛ ተናጋሪ እንጂ አረብኛ ወይም አማርኛ ተናጋሪ አይደሉም። ስለሆነም ወልቃይቴዎች ትግርኛ በመናገራቸው ምክንያት የትግራይ ብሄረሰብ አካል ሊሆኑ እንደማይችሉት ሁሉ አማርኛ የስራና የአስተዳደሩ ቋንቋ በመሆኑ ምክንያት አማርኛ ስለተናገሩ አማራ አይሆኑም። እንዲሁም በጉርብትና ግንኙነት መንገድ አረብኛ ስለቻሉ ሱዳናዊያን ሊሆኑ አይችሉም።

ከላይ ከተጠቀሱት መስፈርቶች አንዱ የስነ ልቦና ተመሳሳይነት ሲሆን፣ ወልቃይቴዎች አማራ ናቸው የሚለው ቡድን የሚያቀርበው የመከራከሪያ ነጥብ፣ "ወልቃይቴዎች በስነ ልቦናዊ ባህርያቸው ከአማራው እንጂ ከትግራዩ ብሄረሰብ ጋር ተመሳሳይነት የላቸውም" የሚል ነው። የአንድ ብሄረሰብ ስነልቦና የሚገለጸው በተለያዩ የባህል ዘርፎቹ ሲሆን፣ የወልቃይት ህዝብ ባህል በአማራው የለቅሶ ስነ-ስርአት፣ ሽለላ፣ ቀረርቶ፣ ዘፈንና እስክስታ ብቻ የተገደበ አይደለም። ባህል ማለት ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍና የህብረተሰብ አባላት የሚጋሩት አጠቃላይ የጋራ ማህበረሰባዊ ቅርስ ነው። እምነቶች፣ ኪነጥበብ፣ ሃይማኖት፣ ልምድ፣ ባህላዊ እሴቶች፣ አለባበስ፣ አመጋገብ፣ ባህላዊ ጋብቻና ፍቺ፣ ባህላዊ የርስትና የውርስ ህግ፣ እንዲሁም ሌሎች በአንድ ላይ ከመኖር የሚፈጠሩና የሚያድጉ የህብረተሰብ ውጤቶች ሁሉ በባህል ጽንሰ-ሃሳብ ውስጥ የሚካተቱ ናቸው። ከላይ በተጠቀሱት የባህል ዘርፎች መሰረት የወልቃይት ባህል ከአማራውና ከትግራዩ ጋር የሚመሳሰልበትና የማይመሳስልበት ሁኔታዎች አሉ። ከትግራይ ብሄረሰብ ጋር የሚመሳሰልው በቀጥታ ሳይሆን በተዘዋዋሪ መንገድ ነው። ይከውም የወልቃይት ባህል የሚመሳሰለው ኤርትራ ነጻነቷን ስትቀዳጅ አብሮ ከተገነጠለው ትግርኛ ከተባለው የከበሳ አካባቢ ብሄረሰብ ባህል ጋር ነው። በቋንቋም ቢሆን የወልቃይት የትግርኛ ዘዬ ወይም ዳያሌክት ተመሳሳይነቱ ከኤርትራ ትግርኛ ጋር ነው። ስለሆነም ወልቃይቴዎች ከአማራውና ከኤርትራው ብሄረ ትግርኛ ጋር ባላቸው ባህላዊ ተመሳሳይነት ምክንያት ስነልቦናቸው የአማራውን እና የኤርትራውን (ትግርኛ ብሄረሰብ) ሊመስል ይችላል። የወልቃይት ባህል እና ብሄራዊ ስነ ልቦና እንደማንኛውም ባህል ቋሚና የማይለወጥ አይደለም።

ስለዚህ ባህሉ ከእነዚህ ሁለት የአጎራባች ብሄረሰቦች ባህሎች ጋር ስለተመሳሰለ ብቻ የራሱ የሆነ ባህል እና ብሄራዊ ስነ-ልቦና የለውም ማለት ስህተት ነው። የወልቃይት ባህል የራሱንና የሌሎችን ባህሎች አጣምሮና አዋህዶ የያዘ ወስብስብ ተፈጥሮ ያለው ነው። ይህ ዓይነቱ ውስብስብነት የወልቃይትን ባህል ልዩና በወልቃይት ህብረተሰብ ዘንድ የሚገኝ ብቸኛ ገላጭ መስፈርት ያደርገዋል።

የቀሩትን መስፈርቶች ወይም መለኪያዎች እንመልከት። የወልቃይት ህዝብ  በአንድ የተካለለ መልክአ ምድራዊ ይዞታ ተቃቅፎና ተረጋግቶ አብሮ የሚኖር ማህበረሰብ ነው። ወልቃይቴዎች የተዋሃደ ምጣኔ ሃብታዊ ትስስር ደረጃ ላይ የደረሱት መዘጋ ወልቃይትን በመሳሰሉ ቆላማ ስፍራዎች በበሬ እያረሱ መኖሪያቸውን በደጋው አካባቢ በማድረግ ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮና በኋላም በግርማዊ ጃንሆይ ዘመን ይኸው ቆላማ የግብርና ኢኮኖሚ ሙሉ ዘመናዊነትን በተላበሰበት ወቅት ነበር። በተለይ የሁመራ ዘመናዊ እርሻ መላውን የወልቃይት ህዝብ በኢኮኖሚ ለማስተሳሰር ችሎ ነበር። የሁመራ እርሻ ባለሃብቶች መነሻቸው ከባላባቱ መደብ ስለነበር በርካታ ዘመዶቻቸውን አሽከሮቻቸውንና የመንደራቸዉን ሰዎች በእርሻ ካምፓቸው ውስጥ የማሳተፍና የመርዳት ልምድ ነበራቸው። ከእነዚህ ሶስት መለኪያዎች አንጻር ሲታይ ወልቃይቴዎችን፣ ወልቃይቴዎች እንጂ አማራ ወይም ትግሬ ሊሆኑ እንደማይችሉ ጎልቶ የሚታይ ሃቅ ነው። ትግርኛ መናገራቸው ብቻውን ትግሬ እንደማያሰኛቸው ከላይ ተገልጿል። በደስታ ጊዜ የሚዘፍኑትና በሃዘን ጊዜ የሚያለቅሱት በአማርኛ ስለሆነ ብቻ አጠቃላይ ስነ ልቦናዊ ባህርያቸው የአማራ ነው ለማለት አይቻልም። ኢትዮጵያዊነት ዥጉርጉርነት እንደመሆኑ ወልቃይቴነትም ይህን ዥጉርጉርነት ከኢትዮጵያዊነት የመኮረጅ ጸባይ ያለው ይመስላል።

የትግራይ ክልል ባለስልጣናት፣ ምንም እንኳን ወልቃይቴዎችንና ትግራዮችን በተግባር እኩል ባይመለከቱም፣ ወልቃይቴዎች የትግራይ ህዝብ አካል ናቸው የሚል አፍአዊ  አቋም ለማራመድ ይሞክራል። ብዙ የወልቃይት ተውላጆች ግን በውስጣቸው አምነውበትም ይሁን ኢጋርን ፍለጋ በአማራነታቸው እንደሚያምኑ ለማሳየት በግልጽ እየወጡ ነው። ቁጥራቸው ቀላል የማይባል ወልቃይቴዎች ደግሞ አማራም ትግሬም እንዳልሆኑ ይናገራሉ። ስለዚህ የወልቃይት ጥያቄ ዘላቂ መፍትሄ ከእነዚህ ሶስት መስመሮች በአንዱ ላይ የሚመረኮዝ ይሆናል።

ከመስመሮቹ ሁሉ አንዱን የመምረጥ መብት የህዝቡና የህዝቡ ብቻ መሆኑ እንዳለ ሆኖ፣ ለአንድ አፍታ እራሳችንን በምናብ በቤተሙከራ ውስጥ እንዳለን እንቁጠርና የወልቃይትን ባህል ግማሽ ድረስ በንጹህ ውሃ እንደተሞላ ብርጭቆ እንቁጠረው። ቀሪውን ግማሽ ባዶ ቦታ በዘይት ብንሞላው፣ ዘይቱ ባህሪውን ሳይቀይር በላይ፣ ውሃውም ውሃነቱ እንዳለ ሆኖ አብረው በአንድ ቋት ምንነታቸውን እንደያዙ ይቀመጣሉ። አሁንም ሙከራችንን በመቀጠል በአይነ ህሊናችን ውህ የያዘውን ብርጭቆ በዘይት ፋንታ በወተት እንሙላው። የውሀው ውሃማ ቀለም ጠፍቶ ወደ ነጫጭባ ፈሳሽ ነገር ይቀየራል። ከውሃው ይልቅ የወተቱ ባህርይ ጎልቶ ይታያል።

የውሃውና ዘይቱ ምሳሌ የወልቃይትና የአማራው ባህል አንዱ ሌላውን የማደብዘዝ ባህርይ ሳይኖረው ለዘመናት የኖሩ መሆናቸውን የሚያመለክት ነው። የወልቃይት ህዝብ በወገራ አውራጃ ስር ሲኖር በቋንቋው፣ በባህሉም ሆነ በልምዱ ምንም ዓይነት ተጽእኖ ሳይደርስበት ዘመናትን አስቆጥሯል። ወልቃይት በጎንደር ክፍለ-ሃገር ወይም አሁን በአማራ ክልል ሰሜን ጎንደር ተብሎ በሚጠራው አስተዳደር ስር በነበረበት ጊዜ የባህል ወይም የዘር ማጥፋት ወንጀል ተነስቶ አያውቅም ነበር። ለዚህ ሁኔታ ሁለት ምክንያቶችን መጥቀስ ይቻላል። አንደኛ በነበረው ገዥ መድብ በኩል ከፖለቲካ ባሻገር የሌላውን ባህል የማጥፋት ጥረት አልነበርም።  ሁለተኛ በአማርኛ ተናጋሪዎቹ ገዥዎችና በትግርኛ ተናጋሪዎቹ ወልቃይቴዎች መካከል ብዙ የቋንቋና የባህል ልዩነቶች ስለነበሩ፣ የባህሎች መደባልቅና አንዱ ሌላውን የመተካት እድል የተመቻቸ አልነበረም።

የውሃውና  የወተቱ መቀላቀል ሙከራ የወልቃይትና የትግራይ ባህሎች ሲቀላቀሉ የሚያስከትለውን ክስተት ያመለክታል። ወልቃይቴዎች ትግሬ ናችሁ ተብለው በትግራይ ነጻ አውጪ ድርጅትና ወደ ትግራይ ክልል ግዛት ውስጥ ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ ከፖለቲካውና ከኢኮኖሚው ባሻገር የወልቃይት ባህል በትግራይ ባህል እየተተካ መምጣቱ በብዙ መድረኮች ግልጽ ተደርጓል። ለዚህ ሁለት ምክንያቶች መሰንዘር ይቻላል። በአንድ በኩል፣ በክልሉ ገዥ ፓርቲ ሆን ተብሎ የወልቃይትን ህዝብ ባህል፣ የቋንቋ ዘዬ (ዳያሌክት)፣ ታሪካዊ ቅርሶች እና ባህላዊ እሴቶችን ለማጥፋት የሚደረግ የተቀነባበረ ሴራ መኖሩ በብዙዎች ዘንድ ይታመንበታል። በሌላ በኩል፣ ትግራይና ወልቃይት በቋንቋ መመሳሰል እና በባህል መቀራረብ ምክንያት ባህላዊ ብረዛው ውስጥ-ለውስጥ በራሱ ግፊት የመስፋፋት ምቹ አጋጣሚ ያገኛል።

የወልቃይትና የወልቃይቴዎች እጣ ፋንታ ከላይ በተጠቀሱት ሶስት እይታዎች ላይ ያጠነጠነ ይሆናል። እነዚህም (ሀ) ወልቃይቴዎች ትግራዮች ናቸው (ለ) ኖ! አማራ ናቸው (ሐ) ኖ! ኖ! ወልቃይቴዎች ወልቃይቴዎች ናቸው፣ በሚሉ አቋሞች ይከፋፈላሉ።

ወልቃይቴዎች ወልቃይቴዎች እንጂ አማራም ትግሬም አይደሉም የሚለውን አቋም የያዘው ክፍል ራሱ ሶስት አማራጮችን ይዞ መቅረብ ይችላል። ወልቃይቴዎች ራሳቸውን የቻሉ ብሄረሰብ ቢሆኑም ከአማራ ጋር እንዳይኖሩ የሚከለክላቸው ህግ የለም። በጽንሰያሳብ ደረጃ ከትግራይ ጋር መኖርም ይችላሉ። ብሄረሰብነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በህዝበ-ወሳኔ ቢፈልጉ ከአማራ ጋር መሆን፣ ቢፈልጉ ከትግራይ ጋር ባሉበት መቀጠል፣ ቢፈልጉም በራስ ገዝነት ለብቻቸው መተዳደር እንደሚችሉ መንገዱ ክፍት መሆን አለበት። ወልቃይቴዎች ራሳቸውን የቻሉ ብሄረሰብ እንደሆኑ የሚያምኑ ዜጎች የሚያቀርቧችውን ሶስት አማራጮች ተግባራዊነት ከተጨባጭ ነባራዊ ሁኔታ ተነስተን ለመተንበይ እንሞክር።

**<u>1ኛ፣ ወልቃይትና ትግራይ</u>**

የትግራይ ነጻ አውጪ ግንባር ቋንቋን መሰረት በማድረግ ወልቃይትን ወደ ትግራይ ያካለለው ቀደም ሲል በተለመው እቅድ መሰረት ነበር። በትግሉ ወቅት በዚህ አካሄድ የሚያምኑ ጥቂት የወልቃይት ተወላጆች ነበሩ። ከዚያም ገዥው ፓርቲ ስልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ በስርአቱ ተመልምለው ያደጉ ወጣቶች መኖራቸው ግልጽ ነው። የወልቃይት አካባቢ በትግራይ ስር የሆነው በህዝቡ ይሁንታና በሰላማዊ መንገድ ስላልሆነ፣ የወልቃይት እጣ ፋንታ መወሰን ያለበት በህዝበ-ውሳኔ መሆኑን ብዙዎች ያምኑበታል። ህዝበ-ውሳኔ ቢደረግ ወልቃይቴዎች እንደ አናሳ ብሄረሰብ በትግራይ ክልል ውስጥ ፈቅደው ሊኖሩ ይችላሉን? ይህ አማራጭ ምን ያህል መዝለቅ ይችላል?

ወልቃይት በትግራይ ክልል ውስጥ ብትቀጥል የተሻለ አማራጭ መሆኑን የሚያሳምኑ ብዙ የመከራከሪያ ነጥቦች አሉ። ቋንቋ ለአንድ ብሄር መገለጫ ከሆኑት መለኪያዎች መካከል ጉልህ ሚና አለው። ምንም እንኳን የተለያዩ ብሄሮች አንድ ዓይነት የመግባቢያ ቋንቋ ስላላቸው ብቻ አንድ ናቸው ባይባልም፣ የትግራይና የወልቃይቴዎች ቋንቋ ትግርኛ መሆኑ በሰላም አብሮ የመኖራቸውን እድል ከፍ ያደርገዋል። በሁለቱ መካከል ከጥንት ጀምሮ የኖረው የጋብቻ ዝምድና ሁለቱም ተቃቅፈው በአንድ ላይ እንዲኖሩ ሚያጠናክር ነው። የወልቃይት ባላባቶችና የትግራይ ባላባቶች ተፈላልጎ በጋብቻ የመተሳሰር ልምድ ነበራቸው። የባላባት አባላት ያልሆኑ ተራ የትግራይ ተወላጆች ደግሞ በግለሰብ ደረጃ ወልቃይት ድረስ እየመጡ በግብርና፣ በንግድና በእጅ ስራ ተሰማርተው ለመኖር ምንም ዓይነት እንቅፋት አጋጥሟቸው አያውቅም ነበር። በተለይም ተወላጅ አግብተው የህብረተሰቡን የመግቢያ ቁልፍ፣ ማለትም የወልቃይትን የትግርኛ ዘዬ፣ አኗኗርና ልምድ ከጨበጡ፣ ህዝቡን መስለው ተዋህደው ለመኖር ጊዜ አይፈጅባቸውም ነበር። በሁለተኛው ትውልድ ላይ ሲደርሱም የትግራይነት ደብዛ ጠፍቶ ፍጹም ወልቃይቴ የመሆን እድላቸው ከማንኛውም ብሄረሰብ የላቀ ነበር። በቋንቋ

ልዩነት ምክንያት ይህ የመዋሃድ ሂደት ለአማርኛና ለሌላ ቋንቋ ተናጋሪዎች ቀላል አልነበረም። ይህ ማለት ግን የአማራው ማህበረሰብ በወልቃይት ምድር ተዋልዶና ተከብሮ በሰላም አልኖረም ማለት አይደለም። በዚያን ጊዜ፣ እንደ አሁኑ የወልቃይት ባህል በአዲስ መጤ የትግራይ ተወላጆች የመበረዝ እድል አልነበረውም። እንዲያውም መጤዎቹ ነበሩ ባህሉን እንደራሳቸው ተቀብለው ሲያስተጋቡ የኖሩት።

ስለዚህ የትግራይ ነጻ አውጭ ግንባር ወልቃይትን ከተቆጣጠረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ያለውን ታሪክ በዜሮ ብናባዛው፣ የህዝበ-ውሳኔው ውጤት ከትግራይ ጋር መኖር የሚሹ ወልቃይቴዎች በሰፊ ልዩነት ሊያቸነፉ መቻላቸውን ያበስር ነበር። ቆይ ግን፣ እንዴት ሆኖ በዜሮ ይባዛል፣ እንዴትስ ይረሳል። ህወሀቶችስ መች ረሱ። "ድሮ ሰብ ድዩ ሞይቱ ትግራዋይ (ሰው ነው የሞተው ወይስ ትግሬ) ስትሉን ነበርና፣ ኑ ተገረፉ! ድሮ ሁመራ ላይ አሰርታችሁ ደሞዝ ከልክላችሁናልና ስትኩራሩበት የነበረውን ለም መሬት ለእኛ አስረክባችሁ ጥፉ! አገራችሁን በጦር መሳሪያ ሀይል ለመያዝ ልንገድላችሁ ስንመጣ ውድ ጀግና ታጋዮቻችንን እያነጣጠራችሁ ገድላችሁብናልና፣ ኑ ተረሸኑ!" ድርጊቶቹ ተፈጽመዋል ከተባሉበት ከሰላሳና ከአርባ ዓመታት በኋል የተረሱ ነገሮች ቢኖሩ የወልቃይት እንግዳ ተቀባይነትና በችግር ጊዜ ደራሽነት ብቻ ናቸው። የወልቃይትን ህዝብ ሰብአዊ ክብር የሚያዋርዱ ጥሰቶችን በዚህ መድረክ ላይ መግለጹ በህዝቦች መካከል አላስፈላጊ ቁርሹ ስለሚፈጥር እዛው ተከድኖ ይብሰል ብለናል። ባጭሩ ግን፣ የወልቃይትንና የትግራይን ህዝብ የሚያስተሳስረው ወፍራም ገመድ ስለተጎመደ አሁን ህዝበ-ውሳኔ ቢደረግ ይህ መሬቱን ተቀምቶ እንደ ሁለተኛ ዜጋ ብቻ ሳይሆን እንደ ጠላት የሚታይ ህዝብ ከማን ጋር መኖርን እንደሚመርጥ ግልጽ ነው። በቋንቋ በባህልና በጋብቻ ትስስር ከአማራው በላይ ከሚቀርበው ከትግራይ ህዝብ ጋር ከመኖር ይልቅ ከዲያብሎስ ጋር መኖርን እንዲመርጥ ይገደዳል የሚሉ ድምጾች በርካታ ናቸው።

<u>**2ኛ፣ ወልቃይትና አማራ**</u>

ሲጀመር ወልቃይት የጎንደር እንጂ የአማራ ሆና አታውቅም። ምክንያቱም በኢትዮጵያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስታት አልነበሩምና። ቢሆንም በአማራ ክልል የሰሜን ጎንደር አካል ለመሆን የሚሹ ወልቃይቴዎች "እኛ ወልቃይቴዎች አማራ ባንሆንም ዝንተ አለም አብረን ከኖርንበት ከጎንደር አማራ ብሄረሰብ ጋር አብረን እንኖራለን" የሚሉ ብዙ ሰዎች አሉ። የሰሜን ጎንደር አካል ለመሆን የሚሻው ሌላው ቡድን የወልቃይት ህዝብ በቋንቋም በባህልም በታሪክም አማራ እንደሆነና ትግርኛውንም በጉርብትና ምክንያት ልክ እንደ አረብኛ እንደተማረው የሚያምን ነው። የዚህ ቡድን አባላት ጭራሽ ትግርኛ የወልቃይት የራሱ የመነጋገሪያ ቋንቋ መሆኑን እስከ መካድ ይደርሳሉ። ወልቃይቴዎች ትግርኛን በጉርብትና ምክንያት የተማሩት ቢሆን ኖሮ የኤርትራ ዘዬ ወይም ዳያሌክት ሳይሆን የትግራዩን ዘዬ ነበር የሚናገሩት። ይህ ማለት ግን ከኢርትራ ትግርኛ ተናጋሪዎች ተምረውታል ማለት አይደለም፣ ምክንያቱም ወልቃይት ከኤርትራ ጋር በተከዜ የሚዋሰነው በአመዛኙ ትግርኛ ተናጋሪ ያልሆኑት ቢንአሚሮች በሰፈሩበት በኩል ነው። ስለዚህ የወልቃይት ትግርኛ ከትግራይም ሆነ ከኤርትራው ትግርኛ በአነጋገር ዘዬ (ዳያሌክት)፣ በስነ ቃላት (ቮካቢውለሪ) በሰዋሰዋዊ አግባብ (ሲንታክስ) እና በይዘታዊ አገባብ (ዲስኮርስ አናሊስስ) ይለያል። የቋንቋው ልዩነት ከዳያሌክት የዘለለ ስለሆነ ራሱን የቻለ ሰፊ ጥናት የሚያስፈልገው መስከ ነው።

ከቋንቋ ልዩነት ሌላ ወልቃይትን ከአማራ የሚያራርቅ ብዙ ግፍ ተፈጽሟል። ወልቃይት በቤገምድርና ስሜን ጠቅላይ ግዛት፣ በወገራ አውራጃ ስትተዳደር በነበረችበት ወቅት፣ የወልቃይቴዎች ኑሮ አልጋ በአልጋ ነበር ማለት አይቻለም። ከጣሊያን ወረራ በፊት አስተዳዳሪዎቿ በሙሉ ከጋይንትና ከደንቢያ የመጡ ነበሩ። ስለሆነም ወቃይቴዎች በራሳቸው ተወላጆች የመመራት መብት ተነፍጓቸው ቆይተዋል። በአጼ ምኒልክ ዘመነ መንግስት እቴጌ ጣይቱ ወልቃይት ጠገዴንና ባጠቃላይ ወገራን ሲወርድ ሲዋረድ ያስተዳድሩ የነበሩትን የወልቃይት ባላባት መሪዎች ከአካባቢው ርቀው አዲስ አበባ

ውስጥ ከቁም እስርነት ባልተናነሰ ሁኔታ እንዲኖሩ አድርገዋል። ለምሳሌ ያህል፣ ፊታውራሪ ሃይለማርያም ጎሹ እና ፊታውራሪ አያና ጎሹ (የጀኔራል አሰፋ አያና አባት) ካዛንችስ ሰፋፊ መሬት ተሰጥቷቸው ይኖሩ ነበር። ወደ ጎንደር ተመልሰው ስልጣን ለመያዝ እስካልሞከሩ ድረስ አዲስ አበባ ውስጥ ተንደላቀው የመኖር እድል ነበራቸው። የእቴጌይቱ ዘመድ ደጃዝማች አያሌው ብሩ አሁን ህወሀቶች እንደሚያደርጉት፣ ወልቃይቴዎች አካባቢያቸውን እንዳያስተዳደሩ ሆን ብለው የራሳቸውን አካባቢ ሰዎች የመሾም ፖሊሲ ነበራቸው። ጣሊያን በባሕከር በኩል ድል እያደረገ ወደ ወልቃይትና ጠገዴ ሲያቀና፣ ከታዋቂው አርበኛ ከደጃዝማች መንግስቱ ጎሹ (ቃብቲያ ላይ የጣልያንን አውሮፕላን መትተው የጣሉ) በቀር እነ ፊታውራሪ ሙላው፣ እነ ፊታውራሪ ተሰማና ሌሎቹ ሚስቶቻቸውንና ጓዛቸውን ጠቅልለው ህዝቡን ለፋሺስት ኢጣሊያ ወታደር አጋልጠው ነበር ወደ አገራቸው የፈረጠጡት። ([https://youtu.be/CA5Lzk_AQhg](https://youtu.be/CA5Lzk_AQhg)) በልማቱም በኩል ቢሆን የወልቃይት ህዝብ ተበድሎ ነበር። በሁመራ ዘመናዊ እርሻ ምክንያት ሲገኝ የነበረው ገቢ ለደብረታቦር ትምህርት ቤት መስሪያና ለሌሎች አካባቢዎች ጥቅም ይውል ነበር። አሁን እንደሚደረገው ማለት ነው።

ታላቁ ወልቃይቴ ባለራእይ መሪ ደጃዝማች አያናእዝጊ በጎንደር መኳንንት ደባ በጭካኔ ከተገደለበት ጊዜ ጀምሮ፣ ወልቃይት የወገራ አውራጃ አካል እያለች በወልቃይት ህዝብ ላይ በረባ ባልረባ ምክንያት ተደጋጋሚ የማጥቃት ዘመቻዎች ተፈጽመዋል። ([https://youtu.be/qV-rJulM3E0](https://youtu.be/qV-rJulM3E0) ) በደጃዝማች አያሌው ብሩ ግዛት ዘመን በወገራ ደጋማና ቆላማ አካባቢ የሚኖሩ አማራዎች በወልቃይት ላይ ወረራዎችና ዝርፊያዎች እንዲያካሂዱ ተደርጓል። የጣልያን ሰራዊት ወዲያው ከወልቃይት እንደወጣ በደጃዝማች ነጋሽ የተመራው ዘመቻ በጣም የከፋ ነበር። ወረራውና ዘመቻው እንደ ባህል ሆኖ፣ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በጠገዴው ተወላጅ በክቡር ቢትወደድ አዳነ መኮንን አስተዳደር ሳይቀር በየምክንያቱ ተመሳሳይ ዘመቻዎች ተካሂደዋል። የቢትወደድ ቃብቲያ ላይ በጥይት መቁሰልና የጀግናው ወጣት አርበኛ ወልቃይቴ የመኮንን በርሄ (ጎንደሬ በጋሻውን ያንብቡ) መገደል ከዚህ ዓይነቱ ዘመቻ ጋር የተያያዘ ነበር። እንዲያ ባይሆንማ አንድ ፍሬ አመጸኛ ግለሰብን ለመያዝ ክቡርነታቸው በሺህ የሚቆጠሩ ታጣቂዎች፣ ሲቪሎች፣ ፖሊስና ጦር ሰራዊት አስከትለው ራሳቸው በገዛጃቸው ወደ አንዲት ትንሽ የወልቃይት መንደር መምጣትና በጥይት ተመትተው ከሞት አፋፍ ላይ መድረስ ባላስፈለጋቸውም ነበር። ዘመቻዎቹ በህዝቡ ኢኮኖሚና ስነልቦና ቀላል የማይባል ተጽእኖ ነበራቸው። ዘማቾቹ ሲመጡ በጭቃ ሹሞቹ አማካኝነት በእያንዳንዱ ቤት ይመሩ ነበር። በዚህ ጊዜ ገበሬው ያረባውን ፍየልና የሚያርሰውን በሬ እያረዱ፣ ቤት ውስጥ የተጠራቀመውን ቅቤና ማር እያወጡ በመብላት በአስተናጋጁ ቤተሰብ ላይ ትልቅ ኪሳራ ያደርሱ ነበር። ምዝበራው አልበቃ ብሎ አባወራውን አባርረው ሚስቲቱን አስገድዶ መድፈር የተለመደ ነበር። ይህ አጸያፊ ድርጊት በቤተሰቡ ላይ የሚያደርሰው የስን አእንሮ ጠባሳና በዚያ ወቅት ልጅ ቢረገዝ ሊፈጠር የሚችለው የአባትነት ጥያቄና ጥርጣሬ ምን ያህል አእምሮን እንደሚያዛባ መገንዘብ አያስቸግርም።

ይሁን እንጂ፣ ከአሁኑ ግፍ ጋር ሲነጻጸር ጎልተው የሚታዩ ልዩነቶች አሉ። አንደኛ፣ ዘማቾቹ መሬቱን ቀምተው ለራሳቸው አላደረጉም። ተጠራርገው መጥተው ተወላጁን ጠራርገው አላስወጡም። ዘማቾቹ ግፋ ቢል የሚቆዩት ለአንድ ሁለት ወር ብቻ ነበር።የሁለቱ በዳዮች ልዩነት የቅኝ ገዥዎችን መንታ ፖሊሲዎች እንድናስታውስ ያደርጋል። ቅኝ ገዥዎች አፍሪቃን ሲቀራነቱ ለፋብሪካና ኢንዱስትሪያቸው ግብአት የሚሆኖ ጥሬ ምርቶችን ወደ አውሮፓ ለማጋዝ ነበር። ፋሺስት ኢጣሊያ ግን ኢትዮጵያንና ኤርትራን የመረጣቸው ለመኖሪያነት ነበር። ፋሺስቶች፣ አስመራ፣ አዲሳባና ደሴን የመሳሰሉ ከተሞች ልክ እንደ ጣልያን ከተሞች ህዝብቸውን እያመጡ ማስፈር ጀምረው ነበር። አስመራ ውስጥ እንደ ፊያት ታግሊየሮ ያሉ ተአምራዊ ህንጻዎች የተሰሩትና ኮምቢሽታቶን ሃበሻ እንዳይረግጣት የተደረገው ከተማዋ እንደ ጆሃንስበርግና ፕሪቶሪያ ለመኖሪያነት ስለተፈለገች ነበር። ባለፈው ስርአት እንደተደረገው፣ የሁመራን ሃብት ለሌሎች ከተሞች ባጀት መደጎሚያ ማድረግ እና በአሁኑ ስርአት እንደሚደረገው የሁመራን የእርሻ መሬትና ከተማይቱን ከወልቃይቴዎች ማጽዳት የተለያዩ ናቸው። ከጠቅላላ ህዝቧ ቁጥር ዘጠና ከመቶ የትግራይ ተወላጆች የሚኖሩባት ሁመራ በአስፋልትና በዘመናዊ ህንጻዎች

ስታጌጥ፣ ከባህከር እስከ ቃብቲያ ያለው አርባ አምስት ኪሎሜትር መንገድ መስራት አልተቻለም። በዚህ ምክንያት ክሳድ ግመልን በመሳሰሉ ገአደገኛ መንገዶች ተሽከርካሪዎች ከነተሳፋሪዎቻቸው በገደል እየተንከባለሉ የብዙ ሰዎች ህይወት አልፏል። የቃብቲያ ነዋሪዎች እነሱን ለመቅጣት የተወሰደ የቂም በቀል እርምጃ እንደሆነ ይወስዱታል። በቃብትያ ሰው እይታ፣ ሁመራ የዘመኑ ኮምቢሽታቶ ናት። ሁለተኛ፣ ወልቃይቴ አባወራዎችን ለስደት ዳርገው ወይም ገድለው ንብረታቸውንና ሚስቶቻቸውን የራሳቸው አያደርጉም ነበር። ሶስተኛ፣ በእያንዳንዱ ወልቃይቴ ዜጋ ህይወት ውስጥ ጣልቃ እየገቡ አኗኗሩን፣ የግል ጉዳዩና ፍላጎቱን፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊ፣ ማህበረሰባዊና ፖለቲካዊ ህይወቱን በመቀየስ "እኛ እንወስንልሃለን" አላሉትም። ጠቅላላ ሁኔታው ሲታይ ቂም ቋጥሮ ለመበቀል የተመቻቸ አልነበረም።

ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት ሀቆች ምክንያት አማራዎች በወልቃይቴዎች ላይ ያደረሱት በደል በታሪክ መዘከሩ ባይቀርም፣ ሁለቱን ብሄረሰቦች የሚያስተሳስረው ገመድ ከመበጠስ የዳነበት ሁኔታ አለ። ይኸውም የወልቃይት ህዝብ እየተገደለ፣ እንደ አውሬ እየታደነ፣ ከቀየው ተፈናቅሎ መጠጊያ ባጣበት በዚያ በጨለማ ወቅት መጠጊያ ያደረገው ጎንደርን ነው። ታዲያ አማራ ነን የሚሉትን ወልቃይቴዎችና አማራም ትግሬም አይደለንም የሚሉትን ወልቃይቴዎች በአቋም አንድ ሊያደርጋቸው የሚችል አንዱ ትልቅ ቁምነገር የጎንደር ውለታ ነው። ጎንደሬ ለመሆን አማራ መሆን ግድ አይለም። የህዝቦች መፈቃቀድ እስካለና የዴሞክራሲ መብት እስከተከበረ ድረስ አማራውም፣ ወልቃይቴውም፣ ቅማንቱም ፈላሻውም በጎንደሬነቱ አብሮ መኖር ይችላል።

የወልቃይት አማራ ማንነት እንቅስቃሴ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተደማጭነትን ያገኘው በሁለቱ ክልሎች መካከል በወሰን ውዝግብና በቅማንቶች ጥያቄ ዙሪያ በተፈጠረው አለመግባባት ምክንያት የብአዴንን ቡራኬ ስላገኘ ብቻ ሳይሆን፣ የህወሀት ባለስልጣናት የህዝቡን እሮሮ ለመስማት ጆሮ ዳባ ልበስ በማለታቸውና የተሳሳተ ፖሊሲና አያያዝ በመከተላቸው፣ ህዝቡ በጣም ቆስሎ ስለቆየ ጭምር ነው። የሰሞኑ ከአስተዳዳሪነት ሙያቸው ተነስተው የነበሩትን ወጣት የውልቃይት ተወላጅ ሹማምንት ወደ ቦታቸው መመለስ የወልቃይት አማራ ማንነት እንቅስቃሴን ተከትሎ የመጣ ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ አይነት የይስሙላ እርምጃ ነው። በተጨማሪም የዚህ ዓይነቱ የማንነት መብት መፍትሄ ለበርካታ አመታት በአካባቢው ተወላጆች የዳያስፖራ ማህበረሰብ አባላት ሲብላላ የቆየ ጉዳይ ነው። ልዩነታቸው፣ አብዛኛው የዳያስፖራ አባል በህገመንግስቱ ተግባራዊነት እምነት የሌለው ሲሁን፣ አማራነትን የሚያቀነቅኑ ወገኖች በህገመንግስቱ አንቀጽ 39 ቁጥር 2 እና 5 በተቀመጠው መሰረት ህጋዊ ጥያቄ አቅርበው ህጋዊ ምላሽ ይጠብቃሉ። በሂደቱ ላይ የአላማ ጽናት፣ የርእዮት ጥራት፣ የመንፈስ ጥንካሬና የመስዋእትነት ዝግጁነት ከሌላቸው የሚመኩባቸው ሃይሎች መንሸራተት ሲጀምሮ መፍረክረክ ሊመጣ ይችላል።

**<u>3ኛ፣ ወልቃይትና ወልቃይቴዎች</u>**

አብዛኝዎቹ ወልቃይቴዎች ራሳቸውን ከአማራውም ሆነ ከትግራዩ ብሄረሰብ የተለዩ አድርገው ቢመለከቱም፣ በኢትዮጵያዊነት ካልሆነ በቀር በብሄረተኝነት አቅጣጫ ማሰብ አይዞርላቸውም። በጎንደሮች ስርወ-መንግስት ዘመን ወልቃይቴዎች የነበራቸው ወሳኝ አገራዊ ሚና ከትውልድ ወደ ትውልድ የተላለፈ የማይደበዝዝ አኩሪ የታሪክ አሻራ ነው። በዚያ ዘመን በምጽዋ በኩል የሚገቡትን የውጭ አገር ዲፕሎማቶችን፣ ወንጌላዊያንንና ባለሙያዎችን ተቀብለው አጅበው ወደ ጎንደር የሚያደርሱና ፈረንጆቹ ወደ አገራቸው ሲመለሱ የሚሸኙ የነገስታቱ ታማኝ ዜጎች ወልቃይቴዎች ነበሩ። የፖለቲካ ተቀናቃኝ ግለሰቦች በግዞት መልክ የሚጠበቁበት አስተማማኝ አካባቢ ወልቃይት ነበር። የጎንደር ነገስታት መዘጋ ወልቃይት ምግላብ ፈረስና ተከዜ አጠገብ ወደከሚገኘው ጫካ ዝሆንና አንበሳ ለማደን ሲሄዱ መንገድ የሚመሩና ስለ አደኑ መመሪያ የሚሰጡ የአካባቢው ተወላጆች ነበሩ። ህዝቡ ዳር ድንበሩን ለመጠበቅ በተጠንቀቅ የሚኖር ስለነበር ግብር አይጣልበትም ነበር። የወልቃይት ህዝብ ዳር ድንበሩን የማስከበር ወታደራዊ ሚና እስከ ግርማዊ

ጃንሆይ መንግስት ድረስ ተሸጋግሮ ድሮ ድርቡሾችን ለመመከት ሲዋደቅ እንደነበረው ሁሉ ከሱዳኖችና ከኢርትራ ነጻ አውጭ ግንባር ሽምቅ ተዋጊዎች ጋር እየተዋጋ አንጸባራቂ ድሎችን ተጎናጽፏል።

አገር ወዳድነት ወይም ኢትዮጵያዊነት በያንዳንዱ ወልቃይቴ ደም ሰርጾ የገባ የማንነቱ መለያ ምልክት ነው። አማራ ኢትዮጵያን በበላይነት ሲያስተዳደር የቆየ ብሄረሰብ ስለነበር፣ የብሄረተኝነትና የተጭቋኝነት ስሜት የለውም። በተመሳሳይ መልኩ፣ ወልቃይቴ ሲባል ከኢትዮጵያዊነት ውጭ ወልቃይቴነት፣ አማራነት፣ ወይም ትግራይነት ተሰምቶት አያውቅም። ምንም እንኳን በወልቃይት ህዝብ ላይ የሚደርሰው አድልዎና ግፍ አብዛኞዎቹን የወልቃይት ልሂቃን የሚያንገሸግሽና የሚያስቆጣ ቢሆን፣ በጠባብነት መልህቅ ወስጥ ላለመግባት የማንነት ሙብት ጥያቄን ከማቅረብ ተቆጥበው ቆይተዋል። ሆኖም በየመድረኩ የህዝባቸውን ሰቆቃ ለዓለም ከማሳወቅ አልተቆጠቡም። አንዳንዶቹም ስርአቱ በሌላ ሲተካ የወልቃይት ችግር አብሮ ሊቃለል ይችላል በሚል ስሌት ከሌሎች ተቃዋሚ ሃይሎች ጋር ተሰልፎ መታገልንና ስርአቱን መገርሰስ እንደ አማራጭ ይዘውታል። የአማራ ክልላዊ መንግስት ባለስልጣናት በተራቸው ግፍ እስካልፈጸሙበት ድረስ የወልቃይት ህዝብ እንደ ክልል ለብቻው ተገንጥሎ የመኖር ፍላጎት የለውም።

ስልጤዎች "እኛ ስልጤ እንጂ ጉራጌ አይደለንም" በሚሉበት ወቅት፣ እንዲሁም አማርኛ ተናጋሪው የቅማንት ህዝብ "እኛ ቅማንቶች እንጂ አማራ አይደለንም" በሚሉበት በዚህ የብሄረተኝነት መንፈስ በሰፈነበት ዘመን፣ ትግርኛ ተናጋሪዎቹ ወልቃይቴዎች "እኛ አማራ ነን" ሲሉ ምን ዓይነት እንደምታ አለው? ምስጢሩ ወልቃይቴዎች እውነት አማራ ስለሆኑ ሳይሆን እንደ ሰፊው የአማራ ህዝብ በኢትዮጵያዊነት ጥልቅ ስሜት የተለከፉ ስለሆነ ነው። የአማራው ብሄረሰብ በተለያዩ የውጭ ተጽእኖዎች ምክንያት የሚወክሉትን ድርጅቶች እየፈጠረ በመጣበት ወቅት (መአድ፣ ሞረሽ፣ በአዴን) ወልቃይቴዎች የቅማንትንና የስልጤን ምሳሌ ለመከተል ያለመከጀላቸው ከማንም ብሄረሰብ በላይ፣ አማራን ጨምሮ ለኢትዮጵያዊነትና ለአንድነት ቀናኢ መሆናቸውን የሚያስረዳ ህያው ምስክር ነው።

<u>ቅድመ ሁኔታና ስታተስ ኮ አንቲ ቤለም</u>

**Status que ante bellum:**

"The term *status quo ante bellum* is a Latin phrase meaning «the state existing before the war». The term is used in treaties to refer to the withdrawal of enemy troops and the restoration of prewar leadership."

ህዝበ-ውሳኔ ማድረግ የጥይቄው መደምደሚያ ሲሆን ከዚያ በፊት ግን መከናወን ያለበት ቅድመ ሁኔታ አለ። እንደሚታወቀው ህወሀት የወልቃይትን አካባቢ ሲቆጣጠር የህዝቡን ይሁንታ አግኝቶ አልነበረም። የወልቃይት ስትያዝ ከደርግ አስተዳደር ራዳር ውጭ ነበረች። የደርግ፣ የኢዲዩ እና የኢህአፓ ታጣቂዎች ገባ ወጣ ሲሉባት የነበረችው ወልቃይት ያለ መንግስት ራሷን በራሷ ስታስተዳድር ቆይታለች። የህወሃት ታጋዮች የወልቃይት መልከአ ምድራዊ ገጽታ ለትግሉ ያለውን ስትራተጂያዊ ጠቀሜት በመገንዘብ አስቀድመው በአስቸኳይ ህዝቡን ለማንበርከክና መሬቱን ለመቆጣጠር ጦርነት ከፍተው ብዙ ደም ሊፈስ ችሏል። ወልቃይትን ለመያዝ እስከተደረገው ጦርነት ድረስ፣ ህዝቡ የሚተዳደረውና ፍትህ የሚያገኘው በአባት ሽማግሌዎች መሪነት ነበር። ስለዚህ ከህዝበ-ውሳኔ በፊት፣ በአለም አቀፍ ህግ መሰረት ከሁሉ በፊት ስታተስ ኮ አንቲ መስፈን አለበት። ስታተስ ኮ አንቲ ወይም ስታተስ ኮ አንቲ ቤለም ማለት ከጋራ ስምምነት በፊት አንድን አወዛጋቢ ቦታ በጦርነት የተቆጣጠረው ሃይል አካባቢውን ከጦርነቱ በፊት በነበረው ሆኒታና በፊት ለነበሩት መሪዎች በማስረከብ ለቆ መውጣት አለበት ማለት ነው። ስለሆነም፣ ህዝበ-ውሳኔው መካሄድ ያለበት

ወልቃይት በሃገር ሽማግሌዎችና በፌዴራል አስተዳደር ሞግዚትነት ስር ሆና ለተወሰኑ ወራት ከቆየች በኋላ መሆን አለበት። ይህ ማለት ደግሞ ከምርጫው በፊት ህወሃትና የትግራይ ክልል አስተዳደር ከወልቃይት ምድር ጠቅልሎ መውጣት ይኖርበታል። የወልቃይት አማራ ማንነት ኮሚቴ አባላትና ደጋፊወቻቸው ከተመደበላቸው ስራ ጎን ለጎን ለስታተስ ኮ አንቲ ቅድመ ሁኔታ መሳካት ትርጉም ያለው ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ከዚያ በኋላ ግን ወሳኙ ህዝቡ እንደመሆኑ መጠን ፍላጎቱን በምርጫ እንዲገልጽ እድል መስጠቱ አማራጭ የሌለው መፍትሄ ነው። የኮሚቴው ስራ ያለ እንቅፋት ሊቀላጠፍ የሚችለው አባት ሽማግሌዎች በሚመሩት ጊዜያዊው የአደራ አስተዳደር ጊዜ ነው። አንድ ህዝብ የዲሞክራሲ መብቱን ተጠቅሞ በአብላጫ ድምጽ የፈለገውን መወሰንና መሆን መቻል አለበት። ስለዚህ ወልቃይቴዎች አማራ ባይሆኑም በአማራ ክልል ውስጥ የመኖር መብታቸው የተጠበቀ መሆን አለበት። በተመሳሳይ መልኩ፣ ትግራዮች ባይሆኑም ምርጫቸው እስከሆነ ድረስ በትግራይ ክልል ውስጥ የመኖር መብት አላቸው።

በማሳሰቢያ መልክ ለማጠቃለል ያህል፣ የወልቃይት ተወላጆች በትግራይ ህዝብ ላይ የጥላቻና የቂም በቀል ስሜት ማሳደር ፈጽሞ የማይገባቸው መሆኑ ግልጽ መሆን አለበት። በማንኛውም መልኩ ሰላማዊና ገለልተኛ የትግራይ ተወላጆችን ኢላማ የሚያደርግ እንቅስቃሴ መወገዝ ይኖርበታል። በድርጅቱና በመንግስት መዋቀር በተለያዩ የስልጣን እርከን ላይ የሚገኙ ግለሰቦች ባመጡት ጦስ ምክንያት ሰፊው የትግራይ ህዝብ መወንጀል የለበትም። በሌላ በኩል፣ የትግራይ ተወላጆችም በወልቃይት ምድር ላይ ያላቸውን የኢኮኖሚና የፖለቲካ የበላይነት ላለማስነካት የማንአለብኝነትና የትምክህት ስሜት ማሳየት አይገባቸውም። ለምሳሌ ያህል የወልቃይት ዳያስፖራ ማህበረሰብ አባላት ሁመራ ላይ መሬት ሊሰጡ በክልሉ ፕረዚደንት ተጋብዘው፣ የእርሻ መሳሪይዎች ገዝተው በአገራቸው መሬት ኢንቨስት ለማድረግ ከመጡ በኋላ አፍንጫችሁን ላሱ ተብለው ሀፍረት ተከናንበው ኪሳራ በኪሳር ሆነው የተመለሱበትን ሁኔታ ያስታውሷል። በዚህ ጊዜ ነበር በሁመራ የሚገኙ አንዳንድ የትግራይ ባለሃብቶች "የነቀልነው እሾህ ተመልሶ እንዳይበቅልብን እነዚህን በርኖሶች አታምጡብን" በማለት ወልቃይቴዎች ከአጽመ-ርስታቸው ተነቅለው እንዲቀሩ ለማድረግ ያላሰለሰ ጥረት ያደረጉት። እንደነዚህ ያሉ አክራሪ ወገኖች ከተግባራቸው መቆጠብ ይኖርባቸዋል።በሁለቱም ወገኖች የሚንጸባረቁ ጽንፈኛ ዝንባሌዎች መወገዝና መወገድ ይኖርባቸዋል። በመሰረቱ ህዝቦች ተግባብተው በፍቅር ለመኖር ከቻሉ የወልቃይት የእርሻ ሃብትና የትግራይ የተፈጥሮ እምቅ የማእድን ክምችት የኢትዮጵያውያን የወል እሴቶች እንደመሆናቸው መጠን ሁለቱም ተመጋግበው የህዝቡን ብልጽግናና የሃገሪቱን እድገት ማረጋገጥ ይችላሉ። የትግራይ ህዝብ ሙስናንና የስልጣን መባለግን በመቃወም በቅርቡ በመሪዎቹ ላይ ቆራጥ እርምጃ እንደወሰደው ሁሉ፣ በወልቃይት ህዝብ ላይ የሚደርሰውን አድልዎና ሰቆቃ በመቃወም በግፉአኑ ወገኖቹ ጎን መሰልፍ የዚህ ፈሪሃ እግዚያብሄር ያልተለየው ታላቅ ህዝብ የሞራል ግዴታ ነው። ወልቃይቴዎች ለህዝቡ ያላቸው አክብሮት፣ ህዝብ ከህዝብ የሚያጣሉ፣ የሚያጋጩ፣ የሚያተራምሱ፣ ባለ ጊዜና ባለስልጣን የሆኑትን ከፋፋይ የትግራይ ተወላጆች አይጨምርም።

አሁን በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ስርአት፣ በበጎ ጎኑ የሚታወቀው በኢትዮጵያ ውስጥ እና ሰላም ባልሰፈነባቸው የአካባቢያችን ቀጠናዎች ሰላምንና መረጋጋትን በማምጣቱ ነው። ከዚህም በተጨማሪ የብሄረሰቦችን ጥያቄ ምላሽ ለማስገኘት የተደረገው ሙከራ አዎንታዊ  ይዘት አለው። ቢሆንም ቀደም ሲል በጋምቤላ፣ በመቀጠልም በቤንሻንጉልና በደቡብ፣ በቅርቡ ደግሞ ጎንደር ውስጥ በቅማንቶችና በአማራዎች፣ በአዲስ አበባ ዙሪያ በኦሮሞዎችና በመንግስት ጸጥታ አስከባሪ ሃይሎች የተቀሰቀሱት ግጭቶች በብሄረሰብ ጥያቄ አፈታት ላይ እና ኢትዮጵያን በቋንቋ ማካለሉ ላይ መሰረታዊ ክፍተቶች እንደነበሩ ያሳያል። የወልቃይት ጥያቄ ከዚህ መሰራታዊ የፌዴራል አወቃቀር ችግር ተለይቶ አይታይም።

ከሀይሉ የሺወንድም